# የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባ ስለሆኑ ሰዎች መብትና በጋብቻ ምክንያት ስለሚገኝ የነዋሪነት ቪዛ ዝርዝር መረጃ

## አላማ

በነዋሪነት ቪዛ ወደአሜሪካን ሀገር የሚጓዙ አብዛኞዎቹ ሰዎች ለጥቃት ተጋላጭ የሚሆኑት የእንጊሊዘኛ ቋንቋ ባለመቻላቸው፤ ከቤተሰብና ወዳጆች ተለይተው የሚኖሩ በመሆናቸውና የአሜሪካ ሀገርን ህጎች በበቂ ሁኔታ ባለማወቃቸው ነው። ከዚህም የተነሳ የነዋሪነት ቪዛ አመልካቾች በቤት ውስጥ የሚደርስባቸውን ጥቃት ለፖሊስ ለማሳወቅም ሆነ ማንኛውንም አይነት እርዳታ ለመጠየቅ አይደፍሩም። ይህም አብዛኞቹን ተጠቂዎች ተጎጂ በሚሆኑበት ግንኙነት ውስጥ እንዲቆዩ ያደርጋቸዋል።

ይህ በራሪ ወረቀት የቤት ውስጥ ጥቃት ምን እንደሆነና በአሜሪካን ህግ ስር ስላሎት መብት መረጃ ይሰጥዎታል። ይህም በአለም አቀፍ የጋብቻ አገናኝ መተዳደሪያ ህግ (International Marriage Broker Regulation Act-IMBRA) መሰረት የአሜሪካን መንግስት በእጮኝነት ወይም በጋብቻ ምክንያት የነዋሪነት ቪዛ ላገኙ የውጭ ዜጋ አመልካቾች በአሜሪካን ህግ ስር ስላላቸው መብት እንዲሁም አሜሪካዊ እጮኛቸው /ባለቤታቸው ከቤት ውስጥ ጥቃት ጋር ወይም ሌሎች ወንጀሎች ጋር በተያያዘ ያላቸውን ታሪክ የተመለከተ መረጃ መስጠት ስላለበት ነው። የዚህ ዋና አላማም የእጮኝነት ወይም የጋብቻ የነዋሪነት ጥያቄ ተጠቃሚዎች ስለሚያልፉበት የቪዛ ሂደት በግንኙነታቸው ውስጥ ጉዳት ቢደርስባቸው እንዴት እርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ ትክክለኛ መረጃ መስጠት ነው።

## የቤት ውስጥ ጥቃት ምንድነው?

ባል ወይም ሚስት ወይም የፍቅር ጓደኛ በሌላኛው አጋር ላይ ዛቻ ወይም አካላዊ ጥቃት የሚያደርስ ከሆነ የቤት ውስጥ ጥቃት ይባላል። ይህም ማንኛውም አይነት አካላዊ ጉዳትን፤ያለፈቃድ የሚፈጸም የግብረስጋ ግንኙነትን፤ በማግለል ወይም በማስፈራራት በስሜት ላይ የሚደረግ ጫናን፤ ገንዘብ ነክ ወይም የነዋሪነት ቪዛን የተመለከተ ዛቻና ማስፈራሪያን ሁሉ ያጠቃልላል። አብኛዎቹ የቤት ውስጥ ጥቃቶች የሚፈጸሙት በወንዶች ሲሆን ተጠቂዎቹም ሴቶችና ህጻናት ናቸው። ሆኖም ግን የቤት ውስጥ ጥቃት በወንዶችም ላይ ሊደርስ ይችላል። የቤት ውስጥ ጥቃት ወሲባዊ ትንኮሳን፤ በህጻናት ላይ የሚደርስ ብዝበዛንና ሌሎች አይነት ጥቃቶችንም ይጨምራል።

ወሲባዊ ትንኮሳ ማለት ማንኛውም አይነት ያለፍቃድ በባል/ሚስት ወይም በሌላ ሰው የሚደርስ ወሲባዊ ድርጊት ነው። በህጻናት ላይ የሚደርስ ብዝበዛ ወይም ጉዳት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

- ድንገተኛ የሆነ አደጋን ሳይጨምር ከተገቢ በላይ ህጻናትን በመቅጣት ወይም በሌሎች ምክንያቶች በህጻናት ላይ የሚደርስ አካላዊ ጉዳት
- ተገቢውን የምግብ፣ የመጠለያ፣ የህክምና እና የቁጥጥር እንክብካቤ አለመስጠት
- ወሲባዊ ጥቃት
- በማስፈራራት እንዲሁም አስፈላጊ ፍቅርና እንክብካቤ በመንሳት የሚፈጠር የስሜት ጫና

በማንኛውም ሁኔታ የቤት ውስጥ ጥቃት፤ ወሲባዊ ትንኮሳና በህጻናት ላይ ጥቃት ማድረስ በአሜሪካ ህግ የተከለከለ ድርጊት ነው። ማንኛውም በአሜሪካን ሀገር ውስጥ ያለ ሰው ዘር፣ ቀለም፣ሀይማኖት፣ ጾታ፣ እድሜ፣ ብሄር ወይም የነዋሪነት ሁኔታው ሳያግደው ከጥቃት የመጠበቅ የህግ ከለላ አለው። ማንኛውም የቤት ውስጥ ጥቃት ተጎጂ የሆነ ሰው የነዋሪኔት ቪዛ ወይም የዜግነት ጥያቄ አመልካች መሆኑ ሳያግደው አስፈላጊውን እርዳታ ማግኘት ይችላል። የነዋሪነት ማመልከቻ አቅርቦ የቤት ውስጥ

ጥቃት ተጎጂ የሆነ ሰው ለነዋሪ የሚደረገውን የህግ ከለላ ለማግኘት ብቁ ነው።

በቤት ውስጥ ጥቃት የሚደርስብዎ ከሆነ አይዞት! ይህ በራሪ ወረቀት የተዘጋጀው አስፈላጊውን እርዳታ እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ እና በጉዳዩ ላይ በአሜሪካን ህግ ስር ስላሎት መብት ለማብራራት ነው።

## የቤት ውስጥ ጥቃት ተጎጂዎች በአሜሪካ ሀገር ስር ያላቸው ህጋዊ መብቶች ምንድን ናቸው?

ማንኛውም በአሜሪካን ሀገር ውስጥ የሚገኝ ሰው የነዋሪነት ወይም የዜግነት ሁኔታው ሳይገድበው በፍትሀብሄርና ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስር የተቀመጡ መሰረታዊ የህግ ጥበቃዎች ይደረጉለታል። በተጨማሪም የቤተሰብ ጉዳዮችን በሚመለከቱ ህጎች ስር የሚከተሉት መብቶች ይኖርዎታል።

- ለእርስዎም ሆነ ለልጅዎ የህግ ከለላ (ጥበቃ) የማግኘት
- የባለቤትዎ ፈቃድ ሳያስፈልግ ህጋዊ ፍቺ ወይም መለያየት የመፈጸም
- በጋብቻ ውስጥ የፈሩ የተወሰኑ ንብረቶችን በጋራ የመጠቀም፤ (በፍቺ ወቅት ፍርድቤቶች በእርስዎና በባለቤትዎ መሀከል የንብረትና የገንዘብ ክፍፍል እንዲደረግ ይወስናሉ።)
- ልጆችን የማሳደግ እና የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት (ከ21 አመት በታች የሆኑ ልጆች ያላቸው ወላጆች አብረዋቸው ለማይኖሩ ልጆቻቸው ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል)

ይህን መሰል የቤተሰብ ህጎች የሚሰጥዎትን መብትና ግዴታዎች በይበልጥ ለመረዳት ከነዋሪነት ጥያቄ አመልካቾች ጋር በቤተሰብ ህግ ላይ የሚሰሩ ጠበቆችን ያማክሩ።

ማንኛዉም የወንጀል ድርጊት የተፈፀመበት ሰው የነዋሪነት ወይም የዜግነት ሁኔታው ሳያግደው ለአስፈላጊ ዕርዳታ ፖሊስ ጋር መደወል ወይም የህግ ጥበቃ ትዕዛዝ ከፍርድ ቤቶች የማግኘት መብት አለው። እርስዎ ወይም ልጅዎ በአደጋ ውስጥ ካሉ 911 ላይ ለፖሊስ ይደውሉ። እጮኛዎ ወይም ባለቤትዎ ወይም ሌላ ሰው የወንጀል ድርጊት እንደፈፀሙ ከተጠረጠሩ በቁጥጥር ስር ሊዉሉ ይችላሉ። ማንኛውም አይነት የደረሰብዎትን ጥቃት እና አካላዊ ጉዳት ጊዜው ያለፈ ቢሆንም እንኳ ለፖሊስ ማሳወቅ ይኖርበታል። ማንኛውም ሰው የነዋሪነት ወይም የዜግነት ሁኔታው ሳይገድበው የወንጀል ድርጊትን ለፖሊስ ማሳወቅ (ሪፖርት ማድረግ) ይችላል።

በተመሳሳይ መልኩ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጎጂ ከሆኑ የጥበቃ ትእዛዝ እንዲሰጥዎ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ። በፍርድ ቤት የተሰጠ የጥበቃ ወይም የክልከላ ትዕዛዝ ጉዳት ያደረሰቦዎት ግለሰብ እንዳይደውልሎት፤በአካል እንዳያገኞት፤እነዳይጠጋዎት ወይንም እርስዎ /ልጅዎ/የቤተሰብ አባልዎት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የሚከለክል ይሆናል። ግለሰቡ የጥበቃ ትዕዛዙን የተላለፈ ከሆነ በቁጥጥር ስር እንዲውል ለፖሊስ ማሳወቅ ይችላሉ። የጥበቃ ትዕዛዝ ለማግኘት ማመልከቻዎን በፍርድ ቤቶች ፤ ፖሊስ ጣቢያዎች፤ የሴቶች መጠልያዎች እና የህግ አገልግሎት መስጫ ቢሮዎች ዘንድ ማቅረብ ይችላሉ። ጥቃቱን የፈፀመው ግለሰብ የወንጀል ክስ በእርሶ ላይ ቢያቀርብ፤የነዋሪነት ወይንም የዜግነት ሁኔታዎ ሳይገድቦት ጠበቃ የማናገር፤ ጠበቃዎ በሌለበት መልስ ያለመስጠት እና ራስዎት የመከላከል መብት ይኖርዎታል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥምዎ የነዋሪነት (ኢሚግሬሽን) ጉዳዮችን እንዲሁም የወንጀል ጉዳዮችን የሚዪዙ ጠበቆችን ማማከር አለብዎት።

## የቤት ውስጥ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለደረሰባቸው ተጎጂዎች በአሜሪካን ሀገር የሚሰጡ አገልግሎቶች ምንድናቸው?

በአሜሪካን ሀገር የወንጀል ድርጊት ሰለባ የሆኑ ሰዎች የነዋሪነት ወይንም የዜግነት ሁኔታቸው

ሳይገድባቸው በመንግስት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚሰጡ የምክር አገልግሎ፣የትርጉም፣የድንገተኛ ጊዜ መጠለያ እና የገንዘብ ድጋፍ እርዳታዎችን ማግኘት ይችላል። የሚከተሉት ስልክ ቁጥሮች ለጥቃት ሰለባዎች ከክፍያ ነፃ የሆነ የ24 ሰዓት እርዳታ የሚሰጡ ባለሙያዎች የሚገኙባቸው ናቸው። በእነዚህ ቁጥሮች ቢደውሉ በቋንቋዎት አገልግሎት የሚሰጡ አስተርጋሚዎች ያገኛሉ። ባለሙያዎቹ በአቅራቢያዎት ያሉ ከክፍያ ነፃ የሆኑ የድንገተኛ ጊዜ መጠለያ፣ የህክምና ዕርዳታ፤ የምክር እና የህግ አገልግሎት ሊያገኙበት የሚችሉበትን ቦታ ይጠቁሞታል።

ብሔራዊ የቤት ውስጥ ጥቃት ማሳወቂያ (ሆት ላይን)

ስልክ- 1-800-799 - SAFE- (1-800-799-7233)

1-800-787-3224 (TTY)

ድህረ-ገፅ www.ndvh.org

ብሔራዊ የወሲባዊ ትንኮሳ ማሳወቂያ (ሆት ላይን)

ስልክ፡ 1-800-656- HOPE (1-800-656-4673)

ድህረ- ገፅ www.rainn.org

የጠፉ እና ለብዝበዛ ተጋላጭ የሆኑ ህፃናት ብሔራዊ ማዕከል

ስልክ 1-800-THE-LOST (1-800-843-5678)

ድህረ- ገፅ www.missingkids.com

የወንጀል ድርጊት ሰለባዎች ብሔራዊ ማዕከል

ስልክ 1-800-FYI-CALL (1-800-394-2255)

1-800-211-7996 (TTY)

ድህረ- ገፅ www.ncvc.org

ማስታወሻ፡- የእነዚህ ድርጅቶች ተልዕኮ ደህንነት እና ጥበቃን የተመለከተ ብቻ ነው።

## የቤት ውስጥ ጥቃት /የወሲባዊ ትንኮሳ/ የሌላ ዓይነት የወንጀል ድርጊት ተጎጂ ብሆን ምን አይነት የነዋሪነት (ኢሚግሪሽን) አማራጮች ይኖሪኛል?

የነዋሪነት ጥያቄ ያቀረቡ እና የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የወሲባዊ ትንኮሳ ወይንም የወንጀል ድርጊት ተጎጂ የሆኑ ግለሰቦች ለራሳቸው ወይም ለልጆቻቸው የነዋሪነት ጥያቄ በሶስት አይነት መንገዶች ሊያቀርቡ ይችላሉ። ይህም ሲሆን ያቀረቡት ጥያቄ ሚስጢራዊነት የተጠበቀ ይሆናል።

ስለዚህም ጉዳት ያደረሰብዎት ወይም ወንጀሉን የፈፀመው ወይም የቤተሰብ አባልዎን ጨምሮ ማነኛውም ሰው ሰላቀረቡት ጥያቄ እንዲያውቁ አይደረግም። ጥያቄዎችን ሊያቀርቡባቸው የሚችሉባቸው ሶስቱ አማራጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

- በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን በሚዳኘው ህግ (VAWA) ስር ህጋዊ ነዋሪነት ለማግኘት የሚቀርብ የግል ማመልከቻ
- የነዋሪነት ማመልከቻ ክልከላ ስረዛ በ (VAWA) ስር
- ለወንጀል ድርጊት ሰለባዎች የሚቀርብ ማመልከቻ (U-Immigration Status)

## ጋብቻን መሰረት ያደረገ የነዋሪነት ፈቃድ የማግኘት ሂደት ምን ይመስላል?

ጋብቻን መሰረት ያደረገ የነዋሪነት ፈቃድ እና ዜግነት የማግኘት ሂደት የተለያዩ ሂደቶችን አልፎ የሚሰጥ ነው። ይህ ሂደት ወደ አሜሪካን ሀገር ለመጓዝ ባገኙት የቪዛ አይነት እና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ይሆናል። ከዚህ በታች ስለ ቪዛ አይነቶች እና እርሶ ስላልዎት ህጋዊ መብቶች ጠቅለል ያለ መረጃ ያገኛሉ።

K-1 (ከነዋሪነት ዉጭ ያለ ሁኔታ-የአሜሪካዊ ዜጋ እጮኛ ለሆነ ሰው) - በዚህ የቪዛ አይነት ስር የነዋሪነት አመልካች ከሆኑ አሜሪካዊ እጮኛዎ ጋር ወደ አሜሪካ ከመግባትዎ በፊት ወይም ከገቡ

በኃላ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ ጋብቻ መፈፀም አለብዎት። ጋብቻውን ከፈፀሙ በኃላ የነዋሪነት ጥያቄውን ካቀረበልዎት አሜሪካዊ አጋርዎ ጋር በመሆን የመደበኛ የነዋሪነት ማመልከቻ ወይም የነዋሪነት ሁኔታ ማስተካክያ (FORM I-865) ማቅረብ አለብዎት። ያቀረቡት ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ የነዋሪነት ሁኔታዎ ከ K ወደ በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ መደበኛ ነዋሪነት ይቀየራል። ይህ በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ የነዋሪነት ሁኔታ ለሁለት አመት የሚቆይ ይሆናል።

የ K-1 ቪዛ ካመለከተሎት አሜሪካዊ ግለሰብ ጋር ጋብቻ ሳይፈፅሙ በአሜሪካን ሀገር ከቆዩ ወይም ከሌላ ግለሰብ ጋር ከተጋቡ የቪዛ ቅድመ ሁኔታውን የተላለፉ በመሆኑ ምንም አይነት የነዋሪነት ህጋዊ ዕውቅና አይኖሮትም። በተጨማሪም ከአሜሪካን ሀገር እንዲለቁ የሚያደርግ የህግ ሊከፈትብዎት እና ሌሎች አይነት ቅጣቶች ሊጣልብዎት ይችላል።

K-3 (ከነዋሪነት ውጭ ያለ ሁኔታ-የአሜሪካዊ ዜጋ ባል/ሚስት ለሆነ ሰው) - ይህ አይነት የቪዛ ፈቃድ ካልዎት የቤተሰብ ቪዛ ማመልከቻዎ (I-130) ፈቃድ እስኪያገኙ በጊዜያዊነት ወደ አሜሪካ መግባት ይችላሉ። የቤተሰብ ቪዛ (ፈቃድ) ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ መደበኛ የነዋሪነት ፈቃድ (ግሪን ካርድ) ማግኘት ይችላሉ። ለዚህም የመደበኛ ነዋሪነት ማመልከቻ ወይም የነዋሪነት ሁኔታ ማስተካከያ (ፎርም I - 485) ማቅረብ አለበት።

ከዚህ ውጭ ያሉ ጋብቻን መሰረት ያደረጉ የነዋሪነት ጥያቄ ያቀረቡ አመልካቾች በአሜሪካን ቆንስላ ቢሮ የተሰጣቸውን መረጃ ሊያዩ ይገባል። ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው ድህረ-ገፅ ላይ ማግኘት ይችላሉ። http://www.uscis.gov

## ከጋብቻ ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ማጭበርበሮች ላይ የሚጣሉ ቅጣቶች ምንድን ናቸው?

ከጋብቻ ጋር የተያያዘ ማጭበርበር የሚፈፅሙ የነዋሪነት አመልካቾች አሜሪካን ሀገርን እንዲለቁ ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል። በተጨማሪም ማነኛውንም አይነት የአሜሪካ ቪዛ ጥያቄ ወደፊት ቢያቀርቡ ውድቅ ሊደረግባቸው ይችላል። ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ማጭበርበር ወንጀለኛ (ጥፋተኛ) ሆኖ መገኘት እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስር እና እስከ 250,000 የአሜሪካን ዶላር ይቀጣል።

## አሜሪካዊ ዜጋ ከሆነ ሰው ጋር ጋብቻ ብፈፅም የማገኘው የነዋሪነት ሁኔታ ምንድነው?

የመደበኛ ነዋሪነት ማመልከቻዎ (ፎርም I - 485) ተቀባይ ሲሆን ጋብቻዎ ከሁለት አመት ላነሰ ጊዜ የቆየ ከሆነ ከአሜሪካን የኢሚጌሬሽን ቢሮ (USCIS) ጊዚያዊ (በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ) የመኖርያ ፈቃድ ያገኛሉ። ይህ ፈቃድ ሁለት አመት ሊሞላው ዘጠና ቀን ሲቀረው እርስዎ እና ባለቤትዎ በጋራ በመኖርያ ፈቃዱዎ ላይ ያለው የሁኔታዎች ገደብ እንዲነሳ ማመልከት አለበት። ለዚህም ጋብቻው በንፁህ ህሊና የተፈፀመ መሆኑን እና ህጋዊ ተቀባይነት እንዳለው ማረጋገጥ ይጠበቅቦታል። በመኖሪያ ፈቃዶት ላይ ያለው የሁኔታዎች ገደብ ከተነሳ በኃላ በአሜሪካዊ የትዳር ጓደኛዎ ላይ መሠረት ያላደረገ የራስዎት መደበኛ የነዋሪነት ፈቃድ ይኖሮታል።

የመደበኛ ነዋሪነት ማመልከቻዎ (ፎርም I - 485) ተቀባይ ሲሆን ጋብቻዎ ከሁለት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ የቆየ ከሆነ የመደበኛ ነዋሪነት ፈቃድ ይሰጥዎታል። ይህን ፈቃድ ሲያገኙ የነዋሪነት ሁኔታዎ በአሜሪካዊ የትዳር ጋደኛዎ ላይ መሠረት ያደረገ መሆኑ ያቆማል።

> በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ የመኖርያ ፈቃድ ያላቸው ነዋሪዎች በፈቃዳቸው ላይ ያለው ሁኔታ እንዲነሳላቸው ከትዳር ጋደኛቸው ጋር በጋራ ማመልከት እነዳለባቸው የሚያስቀምጠው የህግ ድንጋጌ እንዲነሳላቸው (ተፈፃሚ እነዳይሆንባቸው) ፈቃድ ሊጠይቁባቸው የሚችሉባቸው ሶስት አማራጬች አሉ። እነዚህም

1. የሁኔታዎቹ መነሳት ከባድ ችግር የሚያደርስ ከሆነ ወይም
2. ከሞት ውጭ ባሉ ምክንያቶች ጋብቻው ከፈረሰ እና አመልካቹ በሁኔታው ላይ ያለው ገደብ በጊዜው እንዲነሳ ጥያቄ ያቀረበ ከሆነ (ማመልከቻውን በተገቢውን ጊዜ ባለማቅረብ ጥፋተኛ ካልሆነ/ች) ወይም
3. በጋብቻው ወቅት አሜሪካዊ ዜግነት ወይም የመደበኛ ነዋሪነት ፈቃድ ያለው ተጋቢ በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ የነዋሪነት ፈቃድ ያለው አቻ ላይ ጉዳት ወይም የጭካኔ ተግባር ከፈፀመ

ሰስቱ የይነሳልኝ ጥያቄዎች መቅረብ ያለባቸው በ (ፎርም I - 751) ላይ ነው። በተጨማሪም ጋብቻው በንፁህ ህሊና የተፈፀመ እንደሆነ እና እንዳልተጭበረበረ ማረጋገጥ አለበት።

## የውጭ አገር ዜጋ ለሆኑ እና አሜሪካዊ እጮኛ ወይም ባል ወይም ሚስት ያላቸው ግለሰቦች እና ልጆቻቸው መብቶቻቸው እነዴት ሊከበር እንደሚችል ተጨማሪ መረጃ እንዴት ያገኛሉ?

እ.ኤ.አ. በ2005 የፀደቀው አለም አቀፍ የጋብቻ አገናኝ መተዳደርያ ህግ (IMBRA) ጋብቻን መሰረት ያደረገ የነዋሪነት ማመልከቻ ሂደት የውጭ አገር ዜግነት ያላቸውን የአሜሪካዊ ዜጋ እጮኛ ወይም የትዳር ጋደኛ ጥቅም መጠበቅ እንዳለበት ያስቀምጣል። እንዲሁም የአሜሪካን መንግስት የውጭ አገር ዜጋ የሆኑን ጋብቻን መሰረት ያደረገ የነዋሪነት አመልካቾች የቪዛ ጥያቄውን በቀረበላቸው አሜሪካዊ አጋራቸው የጥቃት ሰለባ እንዳይሆኑ የሚረዱ መረጃዎችን እንዲሰጥ ይጠይቃል። የዚህም ምክንያት በእጮኝነት ወይም በጋብቻ ወደ አሜሪካ ለነዋሪነት የሚሄዱ ግለሰቦች የአሜሪካን ህጎችን በበቂ ሁኔታ ስለማያውቁ እና በቤት ውስጥ ጥቃት እንዳይደርስባቸው የሚከላለከል ቤተሰብ ወይም ጓደኛ በቅርባቸው ስለማይኖር ነው። ለዚህም ህጉ ይህ በራሪ ወረቀት በፅሁፍ እንዲሰራጭ እና በውስጡ በአሜሪካን ሀገር እርስዎን ከጥቃት ስለሚከላኩ ህጎች እና አገልግሎቶች ዝርዝር መረጃ እንዲሰጥ ያዛል። በተጨማሪም ህጉ አሜሪካዊ አጋርዎ ተደጋጋሚ የሆነ የወንጀል ታሪክ ካለው ለእርስዎ የሚያቀርበው የእጮኝነት ቪዛ ማመልከቻ ውድቅ እንዲሆን ይደነግጋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ እጮኛዎት የሚያቀርበው የቪዛ ድጋፍ (Sponsorship) ማመልከቻ ቅጂ እና የወንጀል ታሪክ ሁኔታው/ዎ መረጃ ለእርስዎም እንዲደርስ ያዛል።

## አለም አቀፍ የጋብቻ አገናኝን የተመለከተ ጉዳዮች በአሜሪካ መንግስት እንዴት ይስተናገዳሉ?

ጋብቻዎ የሚፈፀመው በጋብቻ አገናኝ ድርጅት በኩል ከሆነ ድርጅቱ የእርስዎን አድራሻ ለአሜሪካዊ ደንበኛው ከመስጠቱ በፊት የእርስዎን ፈቃድ ማግኘት እና ስለግለሰቡ የወንጀል እና ሌሎች ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ መስጠት ይጠበቅበታል። ከ አስራ ስምንት አመት በታች ከሆኑ ይህ አይነቱ ድርጅት ምንም አይነት የጋብቻ ማገናኘት ስራ ከእርስዎ ጋር መፈፀም አይችልም።

## ስለ አሜሪካዊ ዜጋ እጮኛየ ወይም የትዳር ጓደኛየ የሚደርሰኝ የወንጀል ታሪክ መረጃ ብቻውን የእጮኝነት / የጋብቻ ውሳኔ ለማድረግ በቂ ነው?

የጋብቻ አገናኝ ድርጅቱ የሚያቀርብሉት የወንጀል ታሪክ ማህደር የሚዘጋጀው ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት በተሰበሰበ መረጃ እና ደንበኞቹ በነዋሪነት ማመልከቻ ላይ ባሰፈሩት መረጃ መሰረት ነው። የአሜሪካ መንግስት የኢሚግሬሽን መስሪያ ቤት (USCIS) በመላው አሜሪካን የተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች መረጃ (Database Access) ላይኖረው ይችላል። በተጨማሪም አሜሪካዊ እጮኛዎ ወይም የትዳር ጋደኛዎ በህግ ያልታወቀ (ያልተረጋጠ) ጥቃትን የመፈፀም ታሪክ ሊኖረው ይችላል። ስለዚህም የሚደርስዎት

የወንጀል ታሪክ ማህደር የተማላ እና በቂ ላይሆን ይችላል። የጋብቻ አገናኝ መተዳደርያ ህጉ ዋና አላማ አስፈላጊውን መረጃ ማቅረብ ብቻ ሲሆን የጋብቻ/የእጮኝነት ግንኙነቱ ለደህንነትዎ የማያሰጋ መሆኑን መወሰን የእርስዎ ሀላፊነት ነው።

## በአሜሪካዊ እጮኛ/የትዳር አጋር የቤት ውስጥ ጥቃት የደረሰበት ሰው የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባም ሊሆን ይችላል?

አንድ ሰው ከቤት ውስጥ ጥቃት በተጨማሪ ህገ ወጥ የሰው ዝውውርን ለመሰሉ ሌሎች ብዝበዛዎች ተጋላጭ ሊሆን ይችላል። ይህም አስገዳጅ የጉልበት ስራ መስራትን ወይም በንግድ ትርፍ ላይ የተመሰረቱ ወሲባዊ ድርጊቶች ተጠቂ መሆንን ያጠቃልላል።

ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ጉዳይ በተመለከተ እርዳታን በሚከተሉት አድራሻዎች ሊያገኙ ይችላሉ

1. ብሔራዊ የህገወጥ የሰዎች ዝውውር መረጃ ማዕከል
   ስልክ- 1-888-373-7888 (በ7ቱም የሳምንቱ ቀናቶች ለ 24 ሰዓት)
   ድህረ-ገፅ
   www.acf.hhs.gov/trafficking
2. የህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና የሰራተኞች ብዝበዛ ማሳወቂያ ግብረ ሀይል የአሜሪካ ፍትህ መስሪያ ቤት
   ስልክ- 1-888-428-7581 (ከሰኞ - አርብ ጠዋት ከ 3፡00-11፡00)
   ድህረ-ገፅ
   www.usdoj.gov/crt/crim/tpwetf.php

ተጨማሪ መረጃ በድህረ ገፃችን ላይ ወይም ቀጥሎ ባለው ከክፍያ ነፃ ቁጥር ላይ በመደወል ሊያገኙ ይችላሉ።

USCIS ጠቅላላ መረጃ - ከክፍያ ነፃ የስልክ መስመር (በአሜሪካን ሀገር)

1-800-870-3676 ወይም ድህረ ገፃችንን http://www.uscis.gov ብለው ይጎብኙ።